ልደታ ካቶሊክ ካቴድራል ት/ቤት ሚያዝያ / 2012 ዓ.ም
የትምህርት ዓይነት ሂሳብ
3ኛ ክፍለ ጊዜ ሂሳብ ትምህርት የትምህርት መካካሻ
ጥያቄዎች ክፍል 2ኛ

<u>መልመጃ</u>

<u>ገንዘብ መደመር መቀነስ</u>
<u>ገንዘብ</u>
<u>በመጀመሪያ ገንዘብ ማለት ምንድን ነው ?</u>

ሰዎች በመግባባት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎት የገዙበትን የብር ኖቶች ወይም የተለያዩ የሳንቲም ዲናሮች ነው ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የብሮቹን የሳንቲሞችና የሳንቲማቹ የዋጋ መጠን የተለያዩ ናቸው ::

እነዚህ ብሮቹና ሳንቲሞች ስንቲሞች በመንግስት ስር ብቻ የሚታተሙ ናቸው ::

በዚህ መሰረት ባለ መቶ ብር ፣ ባለ ሃምሳ ብር ባለ አስር ብር ባለ አምስት ብር እና ባለ አንድ ብር የወረቀት የብር ኖቶች አሉን :: በሳንተም ደረጃ ደግሞ ባለ አንድ ብር ባለ ሳንብት ሳንቲም ባለ ሃያ አምስት ሳንቲም ባለ አስር ሳንቲም ፣ ባለ አስር ሳንቲም ፣ ባለ አምስት ሳንቲም እና ባለ አንድ ሳንቲም ዲናሮች አሉን ::

አሁን ይህንኑ የማስታወሻ ኖቶች ካነበብን በኃላ የሚከተሉን ምሳሌዎች እንመለከታለን ::

<u>ለምሳሌ</u>

1. አንድ መቶ ብር ኖት ስንት ባለ ሃምሳ ብር ኖት ይሆናል ?

   100 ብር 2ባለ ሃምሳ ብር ኖት ይሆናል ::

   ምክንያቱም 50ብር X 2 = 100 ብር ስለሆነ ነው ::

2. የ50 ብር ኖት ስንት ባለ አስር ብር ኖት ይሆናል ?

   50 ብር =10 ብር + 10ብር +10ብ +10ብ +10ብር += 10ብር X 5

3. የ10ብር ኖት ባለ ስንት አምስት ብር ኖቶች ይሆናል ?

   10ብር ኖት + 5ብር= 5ብር X 2

ስለዚህ ሁለት ባለ አምስት ብር ኖቶች አንድ ባለ አስር ብር ኖት ይሆናል ማለት ነው ::

4. የ5 ብር ኖት ስንት ባለ አንድ ብር ኖት ይሆናል ?

   5ብር =1ብር + 1ብር + 1ብር + 1ብር + 1ብር = 5ብር X 1

5. አንድ የ100 ብር ኖት 10 ባለ 10 ብር ኖት ነው = 10 ብር 10 =100 ብር

6. አንድ የ100 ብር ኖት = 20 ባለ 5 ብር ነው ::

ይህ በእንደዚህ አንጻለ ሆኖ የእያንዳአንዱ የብር ኖቶች 7 ናቸው ::
በላይ በተፃፉት አሀዞች ልክ ዋጋ አላቸው ::
በተጨማሪ እያንዳአንዳቸው የተለያዩ ቀለም ቅርፅ እና ስዕሎች አላቸው ::

## ለምሳሌ

የ1ብር ኖት በስንት የ50 ሳንቲም

1ብር = 100 ሳንቲም ነው ::

ስለዚህ 100 ሳንቲም = 2 X 50 ሳንቲም

= 50 ሳንቲም + 50ሳንቲም( 2 ባለ ሃምሳ ሳንቲም )

= 25 ሳንቲ + 25 ሳንቲም + 25 ሳንቲም + 25 ሳንቲም

= 4 X 25 ሳንቲም = ( 4 ባለ 25 ሳንቲም )ይሆናል ማለት ነው ::

## አስተውል

እነዚህ በጠቅላላ ማንኛውም የመገበያያ ገንዘብ በሙሉ በአገሪቱ መንግስት እውቅና ብቻ ታትመው ገበያ የሚውሉ መሆናቸውን መገዘብ አለብን ::

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ

1. አስር ብር ስንት ባለ አንድ አምስት ብር ኖት ይሆናል ? -

________________________________

2. የ50ብር ኖት ስንት የአስር ብር ኖት ይሆናል ? ________________________________

3. 2 ባለ ሃምሳ ብር ኖት ስንት ባለ መቶ ብር ኖት ይሆናል ?

________________________________

4. ሁለት መቶ ብር ኖት ( 200 ብር ኖት ) ስንት ባለ 50 ኖት ይሆናል ?

_________________________

5. 1000 ( አንድ ሺ ) ብር ኖት ስንት ባለ 100ብር ኖት የሆናል ?

_____________________________

6. አንድ ብር ስንት ባለ 25 ሳንቲም ይሆናል ?___________________________________

7. አንድ ብር ስንት ባለ 50 ሳንቲም ይሆናል ? __________________________________

## የሚከተሉትን የፕሮብሌም ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ

1. የአንድ ሙዝ ዋጋ በ75 ሳንቲም ቢሸጥ የ4 ሙዝ ዋጋ ስንት ብር ይሆናል ?-

______________________

2. አቶ ሰለሞን ገበያ ሄደ ከአቶ አበበ በ1000 ብር ሁለት በጎች ገዛ። አቶ ሰለሞን ለአቶ አበበ ስንት ባለ

መቶ ብር ኖት መክፈል አለበት ?

3. ሀምሳ ሳንቲም ስንት ባለ 25 ሳንቲም ይሆናል ?

4. 2 ብር ኖት ስንት ባለ 25 ሳንቲም ይሆናል ?

5. አራት መቶ ብር ስንት ባለ መቶ ብር ነው ?

## የሚከተሉት ጥያቄዎች ደምር( ሩ )

1. 10 ብር + 25 ብር ________________________________
2. 12 ብር + 5 ብር ________________________________
3. 50 ብር + 16 ብር ________________________________
4. 60 ብር + 40 ብር ________________________________
5. 50 ብር + 50 ብር ________________________________
6. 100 ብር + 200 ብር ________________________________
7. 25 ሳንቲም + 75 ሳንቲም ________________________________
8. 10 ሳንቲም + 40 ሳንቲም
9. 55 ሳንቲም + 25 ሳንቲም ________________________________
10. 10 ሳንቲም + 40 ሳንቲም ________________________________

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች ቀንስ

1. 25 ብር – 10 ብር ________________________________
2. 50 ብር – 40 ብር ________________________________
3. 65 ብር – 15 ብር ________________________________
4. 70 ብር – 20 ብር ________________________________
5. 90 ሳንቲም – 80 ሳንቲም ________________________________
6. 95 ሳንቲም – 15 ሳንቲም ________________________________
7. 100 ሳንቲም – 85 ሳንቲም ________________________________
8. 150 ሳንቲም – 100 ሳንቲም ________________________________
9. 85 ሳንቲም – 45 ሳንቲም ________________________________

10. 75 ሳንቲም – 25 ሳንቲም ______________________________

## የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች መልስ ስጥ

አቶ አበባው ለሁለት ልጆቹ 10 ደብተሮች እያንዳንዳቸው በ3 ብር ከሱቅ ቢገዛ በጠቅላላው ስንት ብር ከፈለ ?______________________________

1. በሳንቲም ሲመነዘር ስንት ይሆናል ? ______________________
2. አልማዝ ከአቶ ሀሰን መደብር 1ኪሎ ስኳር በ15 ብር ፣ 2 ኪሎ ስታ በ30 ብር እና 1 -ኬት ክብሪት በ4ብር ብትገዛ አልማዝ በጠቅላላው ስንት ብር ወጪ አደረገች
3. ሰብለወንጌል ተማሪ ነች ለት/ቤትዋ መመዝገቢያ 40 ብር እና ለግማሽ ዓመት የትምህርት ክፍያ 250 ብር ከፈለች ሰብለወንጌል በጠቅላላው ስንት ከፈለች

## የምዕራፍ ሰባት መጠቃልያ መልመጃ

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ

_______ 1. ሁለት የኢትዮጵያ ብር ኖቶች በቅርጻቸው አንድ አይነት ናቸው ::

_______ 2. የ100 ብር ኖት ከባለ 50 ብር ኖት ጋር እኩል ነው ::

_______ 3. 100 ባለ የ1 ብር ኖቶች በ2 ባለ 50 ብር ኖቶች ሊቀየሩ ይችላሉ ::

_______ 4. 10 ባለ 100 ብር ኖቶች 1000 ብር ይሆናሉ ::

_______ 5. 20 ባለ 5 ብር ኖቶች ከባለ 1 ባለ 100 ብር ኖት ጋር እኩል አይደሉም ::

## ትክክለኛውን መልስ ምረጥ

_______ 1. 2 ባለ 100 ብር ኖቶች ጋር እኩል የሆነው የቱ ነው

ሀ. 4 ባለ 50 ብር ኖቶች ለ. 8 ባለ አስር ብር ኖቶች

ሐ. 10 ባለ 10 ብር ኖቶች መ. መልስ የለውም

_______ 2. ከ10 ባለ 10 የብር ኖቶች ጋር እኩል የሆነው የትኛው ነው

ሀ. 2 ባለ 50 ብር ኖቶች ለ. 4 ባለ 10 ብር ኖቶች

ሐ. 10 ባለ 5 ብር ኖቶች መ. ሁሉም መልስ ናቸው

_______ 3. ከሚከተሉት አንዱ የመመገቢያ ገንዘብ ምድብ አይደለም

ሀ. ብር ለ. ጨው ሐ. ሳንቲም መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስላ

1. የየ5 ብር ኖቶች ስንት የ1 ብር ኖቶች ይሆናሉ ?
2. 10 የ5 ብር ኖቶች ስንት የ1 ብር ኖቶች ይሆናሉ ?
3. 4 የ50 ብር ኖቶች ስንት የ1ብር ኖቶች ይሆናሉ ?

4. **2 የ50 ብር ኖቶች ስንት የ10 ብር ኖቶች ይሆናሉ** ?

5. **4 የ100 ብር ኖቶች ስንት የ50 ኖቶች ይሆናሉ** ?